# በሰላምና ህገ-መንግስቱ ዙሪያ ሀገራዊ መግባባት መፍጠር የዜጎችና የመንግስት መብትም፣ ግዴታም ነው!

## በእምነት ነፃነትና በህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎቻችን ዙሪያ ግልጽነት በመፍጠር ፀረ--ልማትና ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነውን አክራሪነት በዘላቂነት የመዋጋት አስፈላጊነትና ተልእኮዎቻችን

የካቲት 2004

አዲስ አበባ

# በሰላምና ህገ-መንግስቱ ዙሪያ ህገራዊ መግባባት መፍጠር የዜጎችና የመንግስት መብትም፣ ግዴታም ነው!

## I. መግቢያ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህዝበ ሙስሊሙ ውስጥ መነጋገሪያ የሆነ አንድ ጉዳይ ይስተዋላል፡፡ የጉዳዩ አነጋጋሪነት ከጉዳዩ ባለቤቶች አልፎ ባለፉት ዓመታት የአዲስ ራዕይ ዕትሞቻችን ተከታታይ ዕሑፎች የዳሰስናቸውን የከሰሩ ፖለቲከኞችን ትኩረትም ስቧል፡፡ አንዳንዶቹም ዘወትር ውስጥ ውስጡን እያብሰለሰሉ አጋጣሚ ብቻ ለሚጠብቁለት የነውጥ ዓላማቸው አመቺ ሁኔታ እየተፈጠረ እንደሆነ ስለተሰማቸው ምክር፣ ተግሳፅና ብይን ብጤ በመስጠትም በየጋዜጦች፣ በሚያወጧቸው ጹሑፎች የውዥንብሩን አድማስ ይበልጥ ለማስፋት መታተር ጀምረዋል፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ በአመራራችንና አባላት ዘንድ የተሟላ ግልጽነት የለም፡፡ የተሟላ ግልፅነት ባልተያዘበት ሁኔታ በአቋማችንና ተግባሮቻችን ላይ ግልጽነት ፈጥረን ህገ-መንግስታዊ ግዴታችንን እየተወጣን ህዝቡም ተገቢውን ግንዛቤ እንዲይዝ በማድረግ ጽንፈኞችን ማጋለጥና መነጠል አይቻልም፡፡

ከእስልምና እምነት በተያያዘ የተፈጠረውን ወቅታዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በተከታታይ የአዲስ ራእይ ዕትሞች ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ አቅጣጫችንን ይበልጥ እያሰፋን አክራሪነትን የምንዋጋባቸውን አቅጣጫዎችና በኃይማኖት ሽፋን የሚካሄደውን የኪራይ ሰብሳቢዎች አሰላለፍ ያየንበትን ሁኔታ ማስታወስ ይገባል፡፡ በመሆኑም በየደረጃው በአመራሩና አባላት ዘንድ የውይይት መድረኮች ከፍተን መግባባት በመፍጠር ህዝቡን ከብዥታዎች አለወጥተን አክራሪዎችን በማጋለጥ ተባብሮ መንቀሳቀስ ይችል ዘንድ በፊፀምነውና ልንፈጽመው በሚገባን፣ በተናፈሰውና በእውነታው፣ እንደመንግስትና እንደዜጎች በሚመለከተንና ለእምነቱ ባለቤቶችና ተቋሞቻቸው ብቻ መተው ባለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

## II. የበርካታ ዘመናት አድሎና ጨለማ ተገፎ ባለፉት 20 ዓመታት የእኩልነት ብርሃን አይተናል፡፡

በቅርቡ የተከሰተውን መደናገርና ምክንያቶቹን ከመመልከታችን በፊት አጠቃላይ ሁኔታዎች ላይ መግባባት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ለዚሁ እንዲረዳን ሀገራችንና ህዝቦቿ ባለፉት ሥርዓቶች ያለፉባቸውን አስከፊ ሁኔታዎች ከህገ-መንግስታዊ ሥርዓታችንና ያለፉት ሃያ ዓመታት ተጨባጭ ጉዟችን ጋር ማገናዘብ የተሻለ ነው፡፡ ሀገራችን ለበርካታ ዓመታት ዜጎች በሚከተሉት እምነት ብቻ ሳይሆን በደማቸውም ከፍና ዝቅ ተደርገው የሚታዩባት ነበረች፡፡ በየዘመኑ የነበሩ ነገስታት እና የበላይ መሪዎች አንዱን ኃይማኖት ከሌላው

በማበላለጥ ህገ-መንግስታዊ እውቅናና ጥበቃ የነበረው ግፍ ሲፈፀሙ ኖረዋል፡፡ መንግስታዊ ኃይማኖት እንዲኖር በህገ-መንግስት በመደንገግ፣ ኃይማኖትና ትምህርትን በማዋሃድና መሪዎቹ የሚፈልጉት ኃይማኖት የህግ ልዕልና እንዲያገኝ በማድረግ የሌሎች እምነቶች ተከታዮች የሚሸማቀቁበትን ስርዓት በመፍጠር ለበርካታ ዘመናት ህገ-መንግስታዊ ጥበቃ የተደረገለትና እውቅና የነበረው አፈና አስፍነው ቆይተዋል፡፡

የመንግስት ኃይማኖት ከነበረው ውጪ የተለያየ እምነት የነበራቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን በሚከተሉት እምነት ምክንያት የተገለሉበት፣ እንደሁለተኛ ዜጋ የተፈረጁበት ሁኔታ ስለነበር በሀገራቸው ይሁን በራሳቸው ዕጣ ፈንታ የሚወስኑበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ የአቅማቸውን ያህል ለሀገራቸው ዕድገት አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ዕድል እጅግ ጠባብ ነበር፡፡ ዜጎች ተገፍተው እና ተገልለው እንዲኖሩ መደረግ ብቻ ሳይሆን ተገደው እምነታቸውን እንዲቀይሩ የሚደረግበት ዕንፍም ነበረው፡፡

ሀገራችን የራሳቸውን ኃይማኖት ህገ-መንግስታዊ ሽፋን ሰጥተው ይፋ የሃገሪቱ ኃይማኖት አድርገው የሌላውን ያረከሱ መሪዎች የነበሩዋትን ያህል ፀረ-ሁሉም ዓይነት ኃይማኖቶች የነበረዉ የደርግ ሥርዓት ውስጥም አልፋለች፡፡ በእንደዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ደግሞ ተቆው ዜጋ ብቻ ሳይሆን የስርዓቱ ባለሟሎችም በይፋ እምነታቸውን የመግለፅና የማምለክ ዕድል የተነፈጉበት ነበር፡፡ ፀረ-ሁሉም ኃይማኖቶች በነበረው የደርግ ሥርዓት ውስጥ ሁሉም ዜጎች እንደዜጋ የተጨቆኑ መሆኑ አንድ ነገር ሆኖ ቀደም ሲል የነበሩት የአድሎ ሥርዓቶች የፈጠሩት ወጣገባነት እንደተቋምም እንደአስተሳሰብም ተስተካክሎ ነበር ለማለት አይቻልም፡፡

ኃይማኖቶችን በማበላለጥ ገዢዎች ከሚከተሉት እምነት የተለየ ኃይማኖት የሚከተሉ ዜጎች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ በሚታዩባቸውም ይሁን የሥርዓቱ አራማጆች ሳይቀር ነፃነት በተነፈጉበት ፀረ-ሁሉም ኃይማኖቶች በነበረው የደርግ ስርዓት ውስጥ በሀገራችን ዴሞክራሲ ለማስፈንና የዜጎችን የተናጠልና የቡድን መብቶች ለማስከበር ይደረጉ በነበሩ የህዝቦች የትግል አጀንዳዎች ውስጥ እንደመሬት ሁሉ የእምነት፣ የባህልና የቋንቋ እኩልነት መብቶችም ዋናዎቹ ነበሩ፡፡ ስለዚህም ነው ህገ-መንግስታችን እጅግ ዘመናዊ የሚባሉ ህገ-መንግስቶች የያዙዋቸውን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አካቶና አስተማማኝ ዋስትና ሰጥቶ ሲያበቃ የሀገራችን ህዝቦች የዘመናት የትግል አጀንዳ ለነበሩት የቡድን መብቶችም ኃይማኖትን ጨምሮ በግልጽ በተዘረዘሩ ድንጋጌዎች ጥበቃ ያደረገው፡፡

ያለፉት ሥርዓቶች ሲከተሉት የነበረው ኃይማኖቶችን ማበላለጥ፣ ወይም ሁሉንም መደፍጠጥ ሁለንተናዊ ጥፋት መሆኑን በመገንዘብ በሃገራችን የኃይማኖት እኩልነት ተከብሯል፡፡ ህገ-መንግስታችን ኃይማኖት የግል እንደሆነና በኢትዮጵያ የማንኛውም ኃይማኖት ተከታይ ዜጋ ኃይማኖታዊ ደንቡ የሚፈቅደውን ኃይማኖታዊ ስርዓት በነጻነት እንዲተገብር፣ ይህን በማድረጉም ከማንም ወገን አንዳችም ዓይነት ተፅዕኖ እንዳይደርስበት ጥበቃ ያደርግለታል፡፡ በተጨማሪም ለኃይማኖታዊ አድሎ አንድ ወሳኝ መሠረትና ምንጭ የነበረውን መንግስታዊ ኃይማኖት እንዲኖር የማድረግ አሰራር ሙሉ በሙሉ በማስወገድ መንግስትና ኃይማኖት እንዲነጣጠሉ ተደርጓል፡፡ መንግስት በኃይማኖት ኃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ አይገባም፡፡ ህገ-መንግስታችን ኃይማኖትና መንግስት የተለያዩ እንዲሆኑ በመደንገጉ ዜጎች የትኛውን ኃይማኖት ወይም ሴክት መከተል እንዳለባቸው እና በምን መንገድ መከተል እንዳለባቸው መንግስት መወሰንና አቅጣጫ ማስቀመጥ አይችልም፡፡ ኃይማኖቶች ሁሉ እኩል በመሆናቸው መንግስት ብቻ ሳይሆን ዜጎችም በተናጠል አንዱ የሌላውን ሰው ኃይማኖት ወይም በአንድ እምነት ተከታዮች ዘንድም አንዱ የሌላውን ሴክት መወሰን አይችሉም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ኃይማኖትና ትምህርት እንዲሁም ኃይማኖትና ሚዲያ በህግ እንዲለያዩ ተደርጓል፡፡ ስለዚህም ትምህርትን በማስታከክ የአንዱን ኃይማኖት የሌላ እምነት ተከታዮች ተገደው የሚማሩበት ሁኔታ ተወግዷል፡፡ የሁሉም ዜጎች ሀብት በሆነው የመንግስት ሚዲያ የአንዱን ኃይማኖት በማስተማር ለሌላው ዕድል መንፈግ የሚቻልበት ሁኔታ ተወግዷል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በተግባር በመዋላቸው በሀገራችን በኃይማኖቶች መካከል መበላለጥ እንዲኖር እና ከዚያም ተያይዞ ሊቀሰቀስ ለሚችል ቅሬታና ግጭት ምንም ዓይነት ህጋዊና ፖለቲካዊ መነሻ እንዳይኖር ተደርጓል፡፡

የኃይማኖት እኩልነት መደንገጉና፣ ለአድሎና መበላለጥ ምንጭ ይሆኑ የነበሩት ወሳኝ ተቋማት መንግስት፣ ትምህርት እና ሚዲያ ከኃይማኖት እንዲለያዩ ማድረጉ አንድ ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ወሳኝ እርምጃ ተወስዶም ቢሆን በተግባር አድሎ መፈፀም የሚቻልባቸው ሁኔታዎች በተለያዩ ሀገሮች ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ግን ያለፉት 20 ዓመታት ጉዟችን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎቹን ይበልጥ ሥር እንዲሰዱ ተጨባጭ ርብርብ በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ ድርጅታችን ኢህአዴግ በጨለማው ዘመን ውስጥ ሆኖ ለነዚህ መብቶች የተዋደቀላቸው እንደመሆኑ ጨለማው ተገፎ በብርሃን እንዲተካና እነዚህ መብቶች ህገ-መንግስታዊ ዋስትና እንዲያገኙ የአንበሳውን ድርሻ ከመጫወቱም በላይ ባለፉት 20 ዓመታት የህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች

ሳይሸራረፉ እንዲተገበሩና ሥር እንዲሰዱ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡ በማድረግም ላይ ነው፡፡

ቀደምት ሥርዓቶች በተከተሉዋቸው የኃይማኖት ጭቆናዎች ምክንያት የተፈጠሩና ሥር ሰደው የቆዩ የፍትህ መጓደሎችን ለማረምም እጅግ አበረታች እንቅስቃሴ በማድረግ ረጅም ርቀት ተጉዟል፡፡ የእምነት ቦታዎችን ለመገንባት የነበሩ ችግሮችን በመቅረፋችን ባለፉት 20 ዓመታት በሁሉም ኃይማኖቶች ዘንድ የእምነት መዳረሻ ቦታዎች በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት ተስፋፍተዋል፡፡ ኃይማኖታዊ በዓላት ሀገራዊ እውቅና ከማግኘት አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ የመቻቻል ባህላችን ማሳያዎች እንዲሆኑ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡ ሀገ-መንግስታችንን በተግባር ለማዋል የተደረገው ጥረት እንደማንኛውም ጀማሪ ዴሞክራሲ በርካታ የሚሻሻሉና የሚዳብሩ ገጽታዎች እንደሚኖሩት ግልፅ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መሠረታዊ ማዕቀፉን ወይም ሀገ-መንግስታዊ ድንጋጌውን በትክክል ከማስቀመጥ ባሻገር በተግባር ለሁለት አስርተ ዓመታት ሀገራችንን በትክክለኛው ጎዳና ይዘን እየተጓዝን መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡

## III. ሰሞኑን በህዝበ ሙስሊሙ ከተፈጠረው መደናገርና መደናገሩ እንዲፈጠር ከሚረባረቡ ኃይሎች በስተጀርባ ያለው እውነታና የተዛቡ አመለካከቶች፣

**ከየትኛውም ወገን በየትኛውም ሽፋን የሚከሰትን ፅንፈኝነት /አክራሪነት/ ማጋለጥና ስለሰላም ማስተማር የእምነት ነፃነታችን እንዳይሸራረፍ መጠበቅ እንጂ የማንንም እምነት መጋፋት አይደለም!**

### 3.1 አክራሪነትና አፈራረጁ ከልማትና ዴሞክራሲያችን አንፃር እና ከኃይማኖት መሪዎችና አባላት አንፃር

በሀገራችን ሀገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎቹ በሰጡት ዋስትናና ያለፉት ሃያ ዓመታት ጉዟችን ተጨባጭ ስኬት እንዳረጋገጠው ዜጎች የእምነት ነፃነታቸው ተጠብቆ፣ የእምነት መዳረሻዎቻቸው የተስፋፉበት ሁኔታ መኖሩ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ አወንታዊ ሁኔታ በተፃራሪ ከበርካታ አቅጣጫዎች፣ በተለያዩ ሽፋኖች ይህን ምቹ ሁኔታ በመናድ የእምነት ነፃነታችንን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ሰላማችንን ሊያናጉ የሚችሉ አደጋዎችም በዙሪያችን ያንዣብባሉ፡፡ አልፎ አልፎም ህይወትና ንብረት በማውደም በሀገራችን ውስጥም አሻራቸውን አሳርፈዋል፡፡ በአደጋው ምክንያት፣ ምንጭና ስፋት ዙሪያ ግልጽነት መፍጠር በትግል አግባቡ ዙሪያ ለመግባባት ያመቻል፡፡

አክራሪነት/ፅንፈኝነት በፖለቲካ ይሁን በኃይማኖት ሜልኩ የሚገለፅበት፣ ብዙውን ጊዜም ፖለቲካ በኃይማኖት ተለውሶ የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ሰፊ ነው:: በተለይዩ የሀገራችን ክፍሎች፣ በኃይማኖትም ይሁን በፖለቲካ ሽፋን ህይወትና ንብረት ገብረናል:: በኃይማኖትም ይሁን በፖለቲካ እንዲሁም ፖለቲካ በኃይማኖት ተለውሶ ህይወትና ንብረት የጠፋባቸው ክስተቶች በአንድ ኃይማኖት ዙሪያ፣ በአንድ ክልል ወይም የህብረተሰብ ክፍል ዙሪያ ያጠነጠኑና የታጠሩ አልነበሩም፣ አይደሉምም:: በዓለማችንም ሆነ በአህጉራችን የኃይማኖትም ይሁን የፖለቲካ ሽፋን ያላቸው ግጭቶችና ጥፋቶች፣ ምንጮችና አጋሮች መነሻቸው አንድ ኃይማኖት አንድ ሀገር ወይም አህጉር አይደለምና::

ይህን ሁኔታ ለመረዳት በፅንፈኝነት ዙሪያ ያለውን ቅኝት በአጭሩ መመልከት ጠቃሚ ነው:: የችግሩን ምንጭ፣ ስፋትና መገለጫ በማጤን በህብረተሰባችን ውስጥ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መግባባት እንዲፈጠርበት ማስተማር፣ የመታገያ አግባቦች ላይ ግልፅነት መፍጠር የመንግስትና የሁሉም ሰላም ወዳድ ዜጎች ኃላፊነትም ግዴታም ነው:: ችግሩ ከአንድ ኃይማኖት ጋር የተሳሰረ ባለመሆኑ በሚዲያዎች፣ በትምህርት ተቋማት፣ በማንኛውም በርካታ ህዝብ (የአንድ ኃይማኖት ተከታዮች ብቻ ባሉበትም ይሁን ተሰባጥረው) በተገኘበት አጋጣሚ ሁሉ ስለ ህገ-መንግስታችንና ሰላም ማስተማር የማንንም እምነት ማጉደፍ፣ ወይም ማሞካሸት ሊሆን አይችልም:: በመሠረቱ በዓለማችን የሚታወቁ ትላልቅ ኃይማኖቶች ሁሉ ስለፍቅርና ሰላም፣ ስለመቻቻልና አብሮ መኖር የሚሰብኩ ናቸውና:: በአንፃሩ ደግሞ በዓለማችን፣ በአህጉራችንና በአፍሪካ ቀንድ እንዲሁም በሀገራችን በሁሉም ኃይማኖቶች ጥቂት ተከታዮች ዘንድ እምነቶቹን በሽፋንነት ተጠቅሞም ይሁን በፖለቲካ ተለውሶ ከመሠረታዊና ነባራዊ የኃይማኖቶቹ አስተምህሮት ፈንጠር ብለው የሚንፀባረቁ የጽንፈኝነት መገለጫዎች አሉ:: እነዚህን ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ነገር ግን ከኃይማኖቱ መሠረታዊ መመሪያዎች (ቁርዓን፣ መጽሐፍ ቅዱስ) ያፈነገጡ ሆነው ሳለ በኃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ ፅንፈኞችን ማጋለጥ ለሁሉም የእምነት ተከታዮች በአጠቃላይ ለዜጎች የማመን ብቻ ሳይሆን ያለማመን መብታቸውም ጭምር ተከብሮ በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ መፍጠር እንጂ የትኛውንም ኃይማኖት መንካት አይሆንም:: መነሻችንና መድረሻችን ህገ-መንግስታችንን የሚንዱ አደጋዎችን መከላከል መሆኑ::

አክራሪነት /ፅንፈኝነትን/ በማንኛውም ሁኔታ ማጋለጥ አለብን ስንል አፈራረጃችን ላይ እንደአንድ ኃይማኖት ተከታይ ሆነንና እንደአንድ የኢህአዴግ ታጋይ ሆነን የምንፈርጅበት አግባብ ይለያያል:: ስለዚህ ጉዳይ በአዲስ ራዕይ ቅፅ 2 ቁጥር 6 ሀምሌ-

ነሐሴ/2001 ልማት ዴሞክራሲና የኃይማኖት አክራሪነት በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለው ሰፍሮ እናገኛዋለን፡፡

«..... የሃይማኖት አክራሪነት የሚለው አገላለፅ የተለያዩ ሰዎች ከተለያየ መመዘኛ በመነሳት ይተረጉሙታል፡፡ የሃይማኖት መሪዎች አክራሪነትን ከሚመሩት ሃይማኖት መፃህፍት በመነሳት የቅዱሳን መፃህፍቱን መሰረታዊ መርሆዎች የሚፃረር እንደሆነ በዝርዝር ያስረዳሉ፣ ከዚህ በመነሳትም ያወግዙታል፡፡ የሃይማኖቱ እምነት ምን እንደሆነ ከሃይማኖት መሪዎቹ በላይ የሚያውቅ የለምና እነዚህ መሪዎች ከሚያውቁት ነገር ተነስተው አክራሪነትን ቢተነትኑትና ቢያወግዙት መብታቸው ነው፡፡ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ድርጅታችንና መንግስታችን ግን በሃይማኖት ሊቃውንት የተገነቡ ስላይደሉ፣ አንድን ወይም ሌላ ሃይማኖትን ለማራመድ ሳይሆን ሁሉንም ዜጎች በልማትና በዴሞክራሲ ዙሪያ ለማንቀሳቀስ የተደራጁ በመሆናቸው አክራሪነትን የሚመለከቱት ለልማትና ዴሞክራሲ አጀንዳ ካለው ተፅዕኖ በመነሳት ብቻ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ሲታይ የሃይማኖት አክራሪነት ፀረ ልማትና ፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ሆኖ ይገኛል፡፡

የዴሞክራሲ ስርአታችን ሁሉም ዜጎች የእምነት ነፃነት እንዲኖራቸው ያስቀምጣል፣ ዜጎች የራሳቸውን የእምነት ነፃነት ማስከበር ይችሉ ዘንድ የሌላውንም የእምነት ነፃነት ማክበር እንዳለባቸው ያስቀምጣሉ፡፡ አክራሪነት የምንለው ይህንን መሰረታዊ የዴሞክራሲ መርህ በሃይማኖት ሽፋን መቃወም ነው፡፡ ይህ የአክራሪነት አመለካከት በሁሉም ሃይማኖቶች ሊታይ የሚችልና አልፎ አልፎም በተግባር የሚከሰት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ አንዳንድ ሙስሊሞች ሌላው ቀርቶ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሙስሊሞች እንኳ ሳይቀሩ ሃቀኛ ሙስሊሞች አይደሉም ብለው በመፈረጅ የእምነት ተቋሞቻቸውን ለማፍረስ፣ መቃብሮቻቸውን ቆፍረው ለማውደም ይከጅላቸዋል፡፡ የራሳቸውን የእምነት ነፃነት ለማስከበር የሚሞክሩት የሌላውንም ነፃነት በማክበር ሳይሆን የሌላውን ነፃነት በመድፈቅና በማፈን ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ አንዳንድ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ሌላው ቀርቶ የተለየ አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖችም ቢሆኑ የሚከተሉት እምነት ክርስትና አይደለም ብለው ከማመን አልፈው፣ እነዚህ የተለየ አመለካከት ያላቸው ዜጎች እምነታቸውን በነፃነት እንዳያራምዱ በተለያየ ሽፋን ማፈን ይከጅላቸዋል፡፡ ሌሎቹም ሃይማኖቶች ተመሳሳይ አዝማሚያ ሊታይባቸው ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ነገር አክራሪነት በአንድ ሁለት ሃይማኖቶች ብቻ ያልታጠረና አንዱ መሰረታዊ መገለጫው የራሱን የእምነት ነፃነት የሌላን ዜጋ የእምነት ነፃነት በመሸራረፍ በማፈንና በማንቋሸሽ ለማስከበር የሚደረግ መሆኑ ነው፡ ይህ አመለካከት በሃይማኖት ሽፋን የሚካሄድ ፀረ ዴሞክራሲ ነው፡፡ ከፖለቲካ አኳያ ሲታይ የሃይማኖት አክራሪነት የምንለው እንደዚህ አይነቱን አመለካከት ነው፡፡

የዴሞክርሲ ስርአታችን መንግስትና ሃይማኖት መለያየት እንዳለባቸውና አንዱ በሌላው ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት እንደማይገባው በግልፅ ያስቀምጣል:: ይህ ባልሆነበት ሁኔታና ዴሞክራሲ ብሎ ነገር በፍፁም የማይታሰብ መሆኑን ያረጋግጣል:: የሃይማኖት አክራሪነት የምንለው ይህንኑ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መርህ በሃይማኖት ሽፋን መናድ ነው:: ይኸው አመለካከት በተለያዩ መልኮች ሊገለፅ ይችላል:: ስፊ ቁጥር ባይኖራቸውም ጥቂት ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች እንደ ድሮው ሁሉ ኦርቶዶክስ ክርስትና የመንግስት ሃይማኖት እንዲሆን፣ ከሌሎች የተለየ መብትና ጥቅም እንዲኖረው ይመኛሉ:: ይህ አመለካከት ምንም እንኳን በአሁኑ ሰአት በአብዛኛው የከሰመ ቢሆንም አክራሪነት የሚገለፅበት አንዱ ገፅታ መሆኑ አልቀረም:: በሌላ በኩል አንዳንድ ሙስሊሞች የሃይማኖት ብዙህነት ባለበት አገር እነሱው እስልምና ነው ብለው ያመኑበት መመሪያ በመንግስትና በመንግስት ተቋሞች አማካኝነት እንዲፈፀም እስልምና የመንግስት ሃይማኖት እንዲሆን ሲከጅሉ ይታያሉ:: ሌሎችም ሃይማኖቶች ደረጃው ቢለያይም ተመሳሳይ የአክራሪነት ዝንባሌ የተጠናወታቸው አባላት አሉዋቸው ወይም ሊኖራቸው ይችላል::

ከላይ የተጠቀሱት አመለካከቶች ምን ያህል የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ትግላችንን እንደሚፃረሩ ስለሆነም አክራሪነትን የተላበሱ እንደሆኑ ግልፅ ነው:: አክራሪነት የልማት አጀንዳችንን በመፃረር መልክ ይገለፃል:: ከሁሉም ሃይማኖቶች ጥቂት ግለሰቦች ሰርተው በስራ ውጤታቸው ልክ ተጠቃሚ ለመሆን ከመሞከር ይልቅ እምነታቸውን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የተለያየ ጥቅም ለማግኘት፣ ሳይሰሩ ለመክበር በኪራይ ሰብሳቢነት ለመጠቀም ሲገለገሉበት ይታያሉ:: በሃይማኖት ሽፋንም ሆነ በሌላ ሽፋን የሚገለፅ ኪራይ ሰብሳቢነት ፀረ ልማት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው:: በሃይማኖት ሽፋን የሚቀርበውን ይህንኑ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ነው አክራሪነት የምንለው::

የሃይማኖት ዕንፈኝነት የሃይማኖት ሊቃውንት እንደሚሉት የእያንዳንዱን ሃይማኖት መመሪያ የሚፃረር በመሆኑ አክራሪነት ነው:: ግለሰቦች እንደየእምነታቸው የሃይማኖት ሊቃውንቶቻቸው የሚሉትን ተከትለው አክራሪነትን ከሃይማኖታዊ እምነት አኳያ ሊፈርጁት ይችላሉ:: የኢህአዴግ አባላት፣ የመንግስት ሰራተኞችና ሃላፊዎችም በግል የየራሳቸው ሃይማኖት ስለሚኖራቸው ከዚህ ተነስተው በግልና በተናጠል አክራሪነትን ከሃይማኖት አኳያ ሊፈርጁት ይችላሉ:: ኢህአዴግ እንደ ድርጅት፣ መንግስት እንደመንግስት ግን በሃይማኖት ዙሪያ ሳይሆን በልማትና በዴሞክራሲ አጀንዳዎች ዙሪያ የተደራጁ ስለሆኑ አክራሪነትን የሚፈርጁት ከሃይማኖት አኳያ ሳይሆን ከልማትና ከዴሞክራሲ አኳያ ብቻ ነው:: በርግጥ በተግባር ከሃይማኖት አኳያ የሚደረገው የአክራሪነት ፍረጃና፣ ከልማትና ከዴሞክራሲ አኳያ የሚደረገው የአክራሪነት ፍረጃ በውጤቱ እጅግ ተቀራራቢ ወይም አንድ መሆኑ አይቀርም:: ሁለቱ በአስተሳሰብና በተግባር መለየት ግን እጅግ አስፈላጊ ነው:: አንድ የኢህአዴግ አባል

በሙስሊምነቱ ወይም በክርስቲያንነቱ በአክራሪነት ላይ የሚያካሂደው ትግል ከኢህአዴግ ውጪ የሚካሄድና በእምነቱ የሚመራ ይሆናል:: አንድ የኢህአዴግ አባል በኢህአዴግ አባልነቱ በአክራሪነት ላይ የሚያካሂደው ትግል በድርጅት ማዕቀፍ የሚከናወንና ከዴሞክራሲና ልማት መርሆች ብቻ በመነሳት የሚከናወን ነው::»

መንግስት በኃይማኖት፣ ኃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ የማይገቡበትና የሁሉም እምነት ተከታዮች የፈለጉትን እምነት ከመንግስት ይሁን ከሌላ ኃይማኖት ተከታይ ወይም ከራሳቸው ኃይማኖት የአንዱ ሴክት ተከታይም ቢሆን ጫናና አፈና ሳይደርስባቸው በነፃነት የመከተል መብታቸው ሳይሸራረፍ እንደተከበረ እንዲቀጥል በብቃትና በቀጣይነት መታገል ይችሉ ዘንድ፣ ለዚህ መብታቸው መታገልና፣ የሌላውንም መብት ከሌላ ወገን ይሁን ከራሳቸው በሚመነጭ ተግባር አለመደፈሩን የማረጋገጥ ጉዳይ ሳይነጣጠሉ የሚሄዱ መሆናቸው ላይ ግልፅነት መፈጠር አለበት:: በተግባር መገለፅም አለበት:: በሂደትም ባህል እንዲሆን ለማድረግ ህግ ከመደንገግ ያለፈ ተከታታይ ትምህርትና ተግባር ያስፈልጋል:: በመሆኑም የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ መጠቀም ይገባል::

ከየትኛውም ወገን፣ በየትኛውም ዓይነት ሽፋን የሚመጣ አክራሪነት እነዚህን መብቶች በመድፈቅ ብቻ ሳይሆን መብቶቹ ተደፍቀውም ቢሆን በሰላም ወጥቶ መግባት የሚቻልበትን ዕድል የሚያሳጣ መሆኑ ላይ ከየትኛውም ኃይማኖት መሪ ይሁን ተከታይ፣ ከመንግስት አመራር ይሁን ተራ ሠራተኛ ወይም ከገዢ ፓርቲ ይሁን ከተቃዋሚ አባላት ጋር መወያየትና መግባባት የዜጎች የቡድንና የተናጠል መብቶች ተከብረው በቀጣይነት የሚተገበሩበትን ምቹ ሜዳ መጥረግ እንጂ ችግሩ ከአንድ ኃይማኖት ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም:: ትግሉ መሆን ካለበት እንዴት ሁሉንም ዕድሎች አሟጠን እንጠቀም እንጂ ለምን ከሆነ ቦታ ውይይት ተጀመረ ሊሆን አይገባም::

## 3.2 የሰሞኑ የነባሩ የኢትዮጵያ እስልምና አስተምህሮት ስልጠና እና ተያይዞ የተፈጠረው መደናገር

ሰሞኑን የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ለራሱ መዋቅርና ለአንዳንድ የእምነቱ ተከታዮች በሀገራችን የተለያዩ ክልሎች ከተለያዩ ሀገራት በተውጣጡ (እስከአሁን ባለው ሂደት ደግሞ በአብዛኛው ከሊባኖስ በመጡ) ምሁራን በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ዘንድ፣ እስልምና ወደ ሀገራችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ይከተሉታል ተብሎ በሚታመነው ነባሩ የእስልምና ተከታዮች እምነት ዙሪያ ስልጠና በመስጠት ላይ እንደሆነ ይታወቃል:: በሱፊ ይሁን በሌላ የኃይማኖቱ አስተምህሮቶች ዙሪያ ምን ዓይነት ስልጠና መስጠት እንዳለበት የሚወስነውና የወሰነውም መጅሊሱ ነው:: መንግስት እዚህ ላይ

የትኛውን የቁርዓን ክፍል ወይም የትኛውን ፊስግ (መዝሃብ) ማስተማር እንዳለበት የመምረጥ ሚና ሊኖረው አይችልም፣ አልነበረውምም፣ አይኖረውምም:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ በሦስት ጉዳዮች ላይ የተሳሳተ አስተሳሰብ ሰፋ ብሎ ተንፀባርቋል:: ጥቂቶችም ሆን ብለው አዛብተው ህዝቡን ለማደናገር ዘምተዋል::

### 3.2.1 የመንግስትን ሚና በተመለከተ የተነሱ የተዛቡ አተያዮች

ጉዳዩን በትክክል ለመገንዘብ ከስልጠናው ጋር በተያያዘ መንግስት የፈፀማቸውን ሦስት ጉዳዮች ማየት ይጠቅማል:: ሶስቱንም አንድ በአንድ እንመልከታቸው::

#### 3.2.1.1 የስልጠና ስፍራዎችን የማመቻቸት ጉዳይ፣

ለስልጠናው ይመቻሉ ተብለው በመጅሊሱ የተመረጡ ተቋማትን ስልጠና እንዲሰጥባቸው ከመጅሊሱ በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሠረት የማመቻቸትና የመተባበር ሥራ ተሰርቷል:: ይህ የመተባበር ጉዳይ ከመንግስት የተጫነ ዕዳ ሳይሆን በቀድሞ ሥርዓቶች ቢሆን በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ እንኳን ሊጠየቅ ሊታሰብ የማይቻል የነበረ፣ ነገር ግን የሀገራችን ሙስሊሞች እንደሌሎች ኢትዮጵያውያን ህገ-መንግስታችን ያረጋገጠላቸው እምነታቸውን በነፃነት የማጠናከር መብት ነው:: ትያቄ ቢነሳ የማይገርም ሊሆን ይችል የነበረው መንግስት ሳይተባበር ቢቀር ነበር:: ስለዚህም የመንግስት ተቋማትን ለስልጠና እንዲጠቀሙባቸው መፍቀድ አንዱ ተግባር ነው:: ህጋዊና ተገቢ ድጋፍም ነው::

#### 3.2.1.2 የፀጥታና ጥበቃ አገልግሎትን ይመለከታል፣

በማንኛውም ወቅት ሰዎች በርከት ብለው በሚገኙበት ስብሰባ ይሁን ስልጠና በሚኖርበት ጊዜ እንደሚደረገው የፀጥታ አገልግሎት ተሰጥቷል:: እየተሰጠም ይገኛል:: ይህ አገልግሎት ለገዢው ፓርቲ ይሁን ለተቃዋሚዎች፣ ለመንግስታዊ ተቋማት ይሁን ለኃይማኖት ተቋማት የሚሰጥ መደበኛ የመንግስት አገልግሎት ነው:: ይህን አገልግሎት መስጠት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶችና በሀገራችንም የመንግስት ግዴታና የዜጎች መብት እንጂ በዜጎች ላይ የሚደረግ ጫና አይደለም:: ተጠይቆ የሚገኝ ካልተሰጠም ያልሰጠውን አካል በህግ የሚያስጠይቅ አገልግሎት ነው:: ይህን ማድረግ ከስልጠናው ይዘት ጋር ምንም የሚያገናኘው ጉዳይ የለም:: ስለዚህም ኃይማኖቱ በህገ-መንግስታችን የተደረገለትን ጥበቃ የማረጋገጥ ተግባር እንጂ ከሌላው ኃይማኖት በተለየ መንገድ ወይም በኃይማኖቱ ውስጥ አንድን ሴክት የመደገፍ ጉዳይ አይደለም:: ለአንድ ኃይማኖት ህጋዊ ተቋም የተሰጠ ህጋዊ አገልግሎት ነው::

### 3.2.1.3 የመንግስት ግዴታ የሆነው የህገ-መንግስት ትምህርት በየስልጠናዎቹ መጀመሪያ በመንግስት አመራሮች ተሰጥቷል፣

መንግስት ከእምነቱ ጋር በምንም መልኩ በተለየ ሁኔታ ባልተያያዘ ምክንያት የመንግስት መብትና ግዴታም የሆነውን የመንግስት ብቻ ሳይሆን የእስልምና ይሁን የክርስትና ኃይማኖት ተከታዮችን የሚመለከትና እንደዜጋ መብታቸውም ግዴታቸውም የሆነውን የሰላም አስፈላጊነትና ህገ-መንግስት ዙሪያ በየስልጠናዎቹ መግቢያ ላይ አጫጭር ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ወደፊትም መጅሊሱም ሆነ የሌላ ኃይማኖት ተቋማት ተመሳሳይ መድረክ አዘጋጅተው አጋጣሚውን በመንግስት በኩል ይሁን በራሳቸው የሰላምና የህገ-መንግስት ትምህርት እንዲሰጥ እንዲያደርጉ የሚገፋበት ጉዳይ ነው፡፡ በምንም መልኩ ግን መንግስት ኃይማኖት ሊያስተምር አይችልም፡፡ ይህን ተከተሉ ያንን አትከተሉ ማለት አይችልም፡፡ እስከአሁን ባለው ተግባሩም ሆነ ከታገለለት መርህ አንፃር ኢህአዴግም ሆነ በእሱ የሚመራው መንግስት ይህን ሊያደርጉ አይችሉም፡፡ ይህ የሆነበት ሁኔታም የለም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ኃይሎች በሀገራችን የሚያራምዱዋቸውን ፀረ-ህገ መንግስት የሆኑ አቋሞች ከህገ-መንግስቱ ጋር አስተሳስሮ የመግለጽ ጉዳይ ሊኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ ማንም እንደሚያውቀው በእስልምና እምነት ስም የሚንቀሳቀስ ነገር ግን የእስልምና መሠረቶችን ከመናድ ጀምሮ ፀረ-ህገ መንግስት አቋሞች የሚያራምድ ቡድን ኢትዮጵያ ውስጥ አለ፡፡ ይህ ቡድን ካዋርጂያ በመባል ይታወቃል፡፡ በርካታዎቹ መስጂዶች የመቃብር ስፍራዎች የተቃጠሉት በዚህ ቡድን ነው፡፡ ይህ ቡድን ድንቁርናን የሚሰብክ ነው፡፡ ትምህርት አትማሩ፣ ግብር አትክፈሉ እያለ የሚሰብክ ነው፡፡ ሌሎች የእስልምና ተከታዮችንም በኢ-አማኒነት ፈርጆ የሚያጠቃ ነው፡፡ ይህን ጸረ-ሰላምና ፀረ-ህገ መንግስት አቋም ሙስሊሞች ባሉበት ይሁን ማንኛውም ዜጋ በተሰበሰበበት መግለጽ ይቻላል፡፡ የሚገለፀው ከእስልምና አስተምህሮት እንዴት እንዳፈነገጠ በመተንተን አይሆንም፡፡ ይህን የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደድርጅት ወይም እንደመንግስት ባላቸው ኃላፊነት ሳይሆን እንደእምነቱ ተከታይነታቸው ሊያወግዙት ይችላሉ፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮችም፣ የሌላ ኃይማኖት ተከታዮችም በኢህአዴግ አባልነታቸውና በዜግነታቸው ግን ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ሰላም አቋሙን ማጋለጥ መተንተን ይችላሉ፡፡ ይገባልም፡፡

ከከዋርጂያ በተወሰነ ደረጃ የተለየ አቋም ያለው በዚህ ምክንያትም በከዋርጂያዎች ዘንድ እንደ ከሃዲ የሚቆጠረው ወሃቢያ ነው፡፡ ወሃቢያ ከከዋርጂያ በተለየ ሁኔታ በእውቀት፣ በመማር ያምናል፡፡ ከዚህ ውጭ ባለው ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ህገመንግስት

አቋሙ ከከዋርጂያ አይለይም፡፡ ወሃቢያ በመሠረቱ የኃይማኖትና መንግስትን መለያየት አይቀበልም፡፡ ኃይማኖት ከመንግስት ተነጥሎ መሄድ አይችልም፡፡ መንግስትም ኃይማኖትን ማገልገል አለበት የሚል አቋም አለው፡፡ ወሃቢያ በበቀለበት ሳውዲ አረቢያና ቀጥሎ በተስፋፋበት ባህሬን ይህንኑ አቋም የሚያራምድ ነው፡፡ ይኸው አቋሙ እንደኛ በመሰሉ የበርካታ ኃይማኖቶች ቤት በሆኑ ሀገሮች ቀርቶ ሙሉ በሙሉ ሙስሊም በሆኑትም የሺአዎችን፣ የሱፊዎችን ህልውና ህይወት በማጥፋት ጭምር በመፈታተን የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ አቋም ከእስልምና ጋር ምንም ዝምድና የለውም፡፡ ይልቁንም የእስልምና አስተምህሮዎችን ይፃረራል፡፡ ይህ አቋም የፖለቲካ ይዘት ያለው አቋም ነው፡፡ ይህን አቋም መተቸት እስልምናን መተቸት ሊሆን አይችልም፡፡ ኃይማኖትና መንግስት መጣመር አለባቸው የሚል አቋም የራሱን እንጂ የሌላ ኃይማኖትን ቀርቶ ከእስልምና ከራሱ ውስጥ የተለየ ፈለግን የማይቀበል በመሆኑ የለሌላው እምነት ለመድፈቅ የሚንቀሳቀስ ፀረ-ሰላም አቋም ነው፡፡

በእኛ ሀገር ሁኔታ ሆን ብለው ስትራተጂና ታክቲክ ቀይሰው የሚንቀሳቀሱ መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ኃይል በሀገራችን በጣም ትንሽ ተከታይ ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ያለው አብዛኛው ሙስሊም ግን ይህን ፖሊታካዊ ፍልስፍናና አቋም በወጉ ሳያጠና ሀዲስና ቁርዓን ጋር ተያይዘው የሚነገሩትን ገፅታዎች ብቻ ሰምቶ የሚከተላቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አብዛኛው አዋቂ ሰዎች ነባሩን የኢትዮጵያ እምነት የሚከተሉ ዜጎች የወሃቢያዎችን እንቅስቃሴ በአይነቀፋራኛ እንደሚመለከቱ ይታወቃል፡፡ የገንዘብ ምንጩም ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ከሃይማኖታዊ ይዘቱ በመነሳት ሳይሆን ከፀረ-ህገ መንግስት ይዘቱ በመነሳት (ፖለቲካዊ ይዘት ነውና) ፖለቲካዊ ፍረጃ ቢደረግ ኃይማኖትን፣ የእምነት ነፃነትን መጋፋት አይሆንም፡፡

## 3.3 አህባሽ የሚባል አዲስ እስልምና በመንግስት ድጋፍ መጅሊስ አምጥቷል የሚል ተረት

ከላይ የተጠቀሰው ስልጠና የተጠቀሱትን ቡድኖች የተሳሳተ አቋም የማጋለጥ ብቃት ሊኖረው ይችላል፡፡

ይህም በቡድኖቹ ላይ መደናገጥ ፈጥሯል፡፡ ይህ አቋም በይፋ መጋለጥ ሲጀምርም አህባሽ የሚባል የኃይማኖት ዘርፍ ያለ ይመስል፡፡ አህባሽ የሚል አዲስ እምነት መጣብህ በማለት በሀሰት ፕሮፖጋንዳ ህዝበ ሙስሊሙን ማደናገሩን ተያይዘውታል፡፡ ኃይማኖታዊ ይዘቱን መተንተኑ ለእምነቱ ተከታዮች መተው ያለበት ሆኖ ታሪካዊ ገጽታውን ብቻ በማንሳት አህባሽ የሚል አዲስ ኃይማኖት መጥቷል የሚለውን የተሳሳተ ፕሮፖጋንዳ ገለጥ

አድርጎ ማየት ለማንዛቤ ይረዳል:: ሼኽ አብደላ ሀረሪ በነባሩ የኢትዮጵያ እስልምና ፊለግ የጠለቀ እውቀት ከነበራቸው ሰዎች አንዱ እንደሆኑ ይታወቃል:: ይኸው የኢትዮጵያ ነባሩ እምነት ነው በመላው ዓለም ያለው:: ስለዚህም ከመላው ዓለም መምጣት ከሚችሉ ምሁራን ውስጥ ቢያንስ ምንጫቸው ኢትዮጵያዊ የሆኑና በእውቀታቸው በአረቡ ዓለም እውቅና ያገኙት ምሁር ከፊሩዋቸው ምሁራን ማምጣት የተሻለ ይሆናል በሚል እምነት መጅሊሱ እንደሄደበት መገመት አይከብድም::

ወሃቢያ ከሳውዲ አረቢያ፣ ባህሬንና ኦማን ውጭ በሌሎች ሀገሮች ስፋት የለውም:: ከዋረጂያ ከወሃቢያ በፊት ተነስቶና በሺአ እምነት ተከታዮች ተሸንፎ በተወሰነ ደረጃ ሞሮኮ ላይ ሲንቀሳቀስ ቆይቶ በአሁኑ ጊዜ በናይጀሪያ (ቦኮሃራም በሚባል የሚታወቀውና ከፍተኛ እልቂት ፈፅሞ ሰሞኑን በሚዲያ በስፋት እየተዘገበ ያለው) ነው:: በፓኪስታንም ሰፉ ብሎ የሚንቀሳቀስ ነው:: አልሸባብም ለዚሁ ቡድን ቀረበ እንደሆነ ይታመናል:: በሀገራችንም ድሟና ሀረር የተወሰኑ አካባቢዎች የሚንቀሳቀስና በርካታ ጥፋቶች በሙስሊሞች ላይ በማድረስ የሚታወቅ ነው:: ነባሩ ሱፊ ግን በመላው ዓለም ያለ ነው::

ለነገሩ ከየትኛውም ሀገር ምሁር መጥቶ እውቀት ቢሠጥ ነውር የለውም:: በሀገራችን በእስልምናም ይሁን የተለያዩ የክርስትና እምነት ተከታዮች ከተለያዩ ዓለም ክፍሎች የየኃይማኖታቸውን ምሁራን እያስመጡ ሰሚናር ወይም ስልጠና እየሰጡ እንዳለ የሚታወቅ ሲሆን ለወደፊቱም ሊቀጥሉበት እንደሚችሉ ይገመታል:: እስልምናን በተመለከተም በነፃነት የሀገራችን ነባሩ ኡለማዎችም በዚህ ረገድ በወሃቢያዎች እየተዋከቡ እንጂ ማስተማር የሚችሉበት ዕድል ማግኘት ይችላሉ:: እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ አህባሽ የሚባል አዲስ ኃይማኖት ያለ ይመስል ሼህ አብደላ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው አረቦቹ ሀበሻ መሆናቸውን ግንዛቤ በማስገባት አብደላ አልሃባሽ ብለው የጠሩዋቸውን መጠሪያ ይዘው አህባሽ የሚል ኃይማኖት መጅሊሱን ተጠቅሞ መንግስት አምጥቷል በማለት አክራሪ ኃይሉ ዘመቻ የከፈተው:: ይህ ዘዴ የእምነቱ ተከታዮች ተገቢውን እውቀት ካገኙ ለአክራሪ አቋም የማይሆን ምቹ ሁኔታ እንደሚጠፉ በመገንዘብ አስቀድሞ አቧራ ለማስነሳት የተጠቀሙበት ዘዴ ነው::

## 3.4. ከአወሊያ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው ሁኔታ እና ይህን ተከትሎ በተወሰኑ ቡድኖች ተነስተው በርካታዎችን ያሳሳቱ የተሳሳቱ አቋሞች

### ከትልቁ ስዕል ግርጌ ያለች ትንሽ ነቁጥ!

አጠቃላይ ሁኔታው፣ ግርታውና አውነታው ከላይ በአጭሩ ለመጥቀስ የተሞከረው ነው:: የእስልምና ኃይማኖት ተቋሙ ህገ-መንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ ህዝበ ሙስሊሙን

ትክክል ነው ብሎ በማነው መንገድ ለማንቃት፣ መንግስት ደግሞ ህገ-መንግስታዊ ግዴታዎቹ የሆኑትን አገልግሎቶች በመስጠት ምቹ ሁኔታ የመፍጠርና አጋጣሚውን ስለ ሰላምና ህገ-መንግስቱን በማስተማር ለሁሉም የሚጠቅም ተግባር ለመፈጸም የተጠቀመበት መሆኑ ተገቢና ትክክል ነው። ይህ ነው የሚባል የህገ-መንግስትና የህግ ጥሰት ችግር ያልነበረው ቢሆንም ከላይ በገለጽናቸው ምክንያቶች በርካታ ብዥታዎች ተፈጥረዋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው አሁንም መጅሊሱ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ተቋም እንደመሆኑ የአወሊያ ተቋምን በተመለከተ በሰልጣኑ ስር መስራት አለብኝ ብሎ ያመነባቸውን አንዳንድ እርምጃዎችን የወሰደው። ይህ ሁኔታ አስቀድሞ ውዥንብር ውስጥ እንዲገባ የተደረገው የከተማዋ ነዋሪ ለተጨማሪ ብዥታ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የተፈጠረ የመሰላቸውንና ከላይ በገለጽነው መንገድ ከሀገር ውስጥ አልፎ በየአህጉሩ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በከፍተኛ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ሲያምሱ የነበሩ ኃይሎችን ትኩረት የሰባው። በእርግጥ ይህ ጉዳይ ጽንፈኝነቱን ከኋላ በሞራልም በቁሳቁስም ሲደግፍ የነበሩ አሁንም በመደገፍ ላይ ያሉ አንዳንድ የውጭ ኃይሎች የ24 ሰዓት ምክርና አመራር ያልተለየው በመሆኑ የአለም አቀፍ የጽንፈኝነት ኃይሎችን ተሳትፎም አላጣም። የሀገራችንን አንቱ የተባሉ የነውጥ አማልክትን ጨምሮ።

በርከት ያሉ የከተማችን ሙስሊም ነዋሪዎች በተካሄደው ዘመቻ ተደናግረው በእርግጥም ኃይማኖታቸውን እየታደጉ እየመሰላቸው ወደ አወሊያ የተመሙበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም በሂደት በተለይ አዋቂዎች ራሳቸውን ማራቅ ጀምረዋል። በርካታዎቹ ለመቀስቀሻነት ጥቅም ላይ ውለው የነበሩት የመጅሊሱ እርምጃዎች ታርመው የነበረ መሆኑና ህዝቡም ተጨማሪ መረጃዎችን እያገኘ በሄደ ቁጥር ተቋሙ እንድም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሠረት እንዲንቀሳቀስ፣ ሁለትም ለህዝበ ሙስሊሙ የተሻለ አገልግሎት መስጠት በሚቻልበት ደረጃ እንዲስፋፋና እንዲሻሻል የሚደረግበት እንጂ እንደተቀሰቀሰው መንግስት የሚወርስበት ሁኔታ አለመኖሩን እየተረዳ መጥቷል። ይህ በሆነ ጊዜ በአወሊያ አካባቢ የነበረው መሰባሰብ እየቀነሰ መጥቷል። ነባሩንና የተደበቀውን ፀረ-ህገ-መንግስታዊ የሆነውን አቋማቸውን በንፁሃኑ ሙስሊሞች ትርምስ ለማስፈጸም ያሰፈሰፉት ኃይሎች ግን ግርግሩን ከአወሊያ በማስፋት ወደ ሌሎች ታዋቂ መስጂዶች ለማዛመት ሞክረዋል። ህዝበ ሙስሊሙ ግን በተለመደው እርጋታና ጨዋነት በሰላም ሀሉቱን አድርሶ ወደ ጉዳዩ ከመሄድ በስተቀር የሴራው ተካፋይ መሆን አልፈለገም። በዚህ የህዝቡ አቋም በመበሳጨት የተወሰኑት ረብሻውን ራሳቸው ለመለኮስ ሞክረዋል። ተነጥለው እየቀሩ ተቸገሩ እንጂ።

ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ሦስት የተሳሳቱ አቋሞች ተንፀባርቀዋል፡፡

ሀ/ መጅሊሱ ሙስሊሙን አይወክልም፣ ስለዚህም መንግስት ያስወግደው፣ (ጣልቃ ይግባ፣)

ለ/ መጅሊሱ የሚሰጠውን ትምህርት ያቁም፣ (መንግስት ለመማር የሚፈልጉትን መብት በመንፈግ ያስቁም፣ ስለዚህም ጣልቃ ይግባ)

ሐ/ መጅሊሱ ከአወሊያ እጁን ያንሳ የሚሉ ናቸው፡፡

**እያንዳንዳቸውን በአጭሩ መቃኘት ከጉዳዩ በስተጀርባ ያሉትን ኃይሎች የተዛባ መነሻ ለመረዳት ያግዛል**

አንደኛውን አቋም ወስደን ካየን በመሰረቱ ከህገ-መንግስቱ ብቻ ሳይሆን ከሁለተኛው አቋምም ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ መጅሊሱን የማንሳት፣ የመምረጥ፣ የመሾር ጉዳይ የህዝበ ሙስሊሙ ነው፡፡ የመንግስት ድርሻ አይደለም፡፡ በህዝበ ሙስሊሙ እንቅስቃሴ ሙስሊሙ በፈቀደው መንገድ መምረጥ ይችል ዘንድ መንግስት የተለመደውን ሁኔታዎች የማመቻቸት ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ቀደም ሲል ይኸው ኃይል አለአግባብ ነው ብሎ ያዘመተበትን ሁኔታዎችን የማመቻቸት ድጋፍ ማለት ነው፡፡ መጅሊሱ እየሰጠ ባለው ስልጠና ዙሪያ ይህንኑ የመንግስት ድጋፍ ነው ይኸው ኃይል መንግስት በእስልምና ጣልቃ ገብቷል እያለ ዘመቻ የከፈተው፡፡ ይህን የሚል አንደበትና አቋም ያለው ኃይል ተመልሶ ያውም ህገ-መንግስቱ ያልሰጠውን ስልጣን ተጠቅሞ መንግስት መጅሊሱን ያፍርስልኝ የሚል ጥያቄ ያነሳው፡፡ ለዚህ ኃይል መጅሊሱ ስላልተመቸው መንግስት ቢያፍርሰው ህገ-መንግስት መጣስ፣ በእምነት ላይ ጣልቃ መግባት አይሆንም፣ የመንግስት ግዴታ የሆነውን ድጋፍ ማድረግና የመንግስት ግዴታ የሆነውን ህገ-መንግስት የማስተማር ጉዳይ ግን ህገ-መንግስቱን መፃረር ሆኖ ይሰማዋል፡፡ በምድርም በሰማይም የማይታረቅ አቋም ማለት ይህ ነው፡፡ —

ሁለተኛው መጅሊሱ እየሰጠ ያለውን ስልጠና መንግስት ያስቁምልን የሚለው ነው፡፡ ጣልቃ አይግባብን፣ የፈለግነውን አቋም ፀረ-ህገመንግስት የሆነውን ጭምር በነጻነት ማስተጋባት አለብን የሚል ኃይል ባለ በሌለ አቅሙ ስፍራ ጠበበኝ እያለ ምድር ሰማዩን በሀሰት ፕሮፓጋንዳ በሞላበት ሁኔታ መንግስት ከመስመሩ ወጥቶ ህገ-መንግስቱን ጥሶ የአንድ ኃይማኖት ይፋዊ ህጋዊ ተቋም የሆነው መጅሊስ ለእምነቱ ተከታዮች እየሰጠ ያለውን ስልጠና ግን መንግስት እንዲያስቆም የሚጠይቅ ነው፡፡ ስልጠናውን መውሰድ አለመውሰድ፣ ስልጠናውን ከወሰደ በኋላ ማመን አለማመን የተከታዩ ፈንታ ነው፡፡ የመንግስት ሥራ አይደለም፡፡ የመንግስት ስራ እንደ ህጋዊ ተቋም የጠየቀውን ድጋፍ በህግ አጥር ውስጥ ሆኖ መስጠት ነው፡፡

ሦስተኛው ጉዳይ መጅሊስ ከአወሊያ እጁን ያንሳ የሚለው ነው፡፡ መጅሊሱ ድክመት አለበት ብሎ መተቸት ይቻላል፣ መጅሊሱ መጠናከር አለበት ማለት መብት ነው፣ መጅሊሱ በሰፊ የእምነቱ ተከታዮች በየወቅቱ መመረጥ አለበት ማለትም ችግር የለበትም፡፡ የአወሊያ ተቋም ለሙስሊሙ የተሻለ አገልግሎት መስጠት በሚቻልበት ደረጃ መደራጀት አለበትና የተሻለ አመራር የተሻለ ስትራተጅ ሊኖረው ይገባል ማለት ምንም ነውር የለውም፡፡ ተቋሙን የተሻለ አገልግሎት መስጠት በሚችልበት ደረጃ ለማሰደግ መንግስት ድጋፍ መስጠት አለበት ማለትም መብትና ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ነው የሚባል ህግ ያልነበረው፣ ተጠያቂነት ያለበት ኃላፊ ያልነበረው፣ የሀገሪቱን ህጎች አክብሮ የተሻለ አገልግሎት መስጠት የሚችልበት ቁመና ያልነበረውን ተቋም፣ በውጭ ሀገር ሰዎች እንደፈለገው ሲተራመስ የነበረን ተቋም ወደነበረበት ይመለስ ማለት ግን ጤንነት አይደለም፡፡ ለማንም የሚጠቅምም አይደለም፡፡

እርግጥ ህግ አልባ በነበረባቸው ጊዜያት ህገወጥ ተግባር ለመፈፀም የሚቻልበትም ዕድል ነበር፡፡ ስለዚህ አወሊያ ለሙስሊሙ የተሻለ አገልግሎት ይስጥ፣ የሙስሊሙ ተቋም የሆነው መጅሊስም አወሊያን ብቻ ሳይሆን መላውን የሙስሊሙን ጉዳዮች በብቃት የሚመራበት ቁመና ይኑረው የሚል አቋም መያዝ የእምነቱ ተከታዮች መብት ነው፡፡ በዚህ አቋም ምንም ችግር የለበትም፡፡ ችግሩ ህጋዊና ተገቢውን ጥያቄ ኢ-ህገ-መንግስታዊ በሆነ መንገድ ለማስፈፃም መሞከር፣ እንዲፈፀምም መጠየቅና በግልፅ የመንግስት ግዴታ ሆኖ እያለ መንግስት ይህን ግዴታውን መወጣቱን ደግሞ ህገ-መንግስት እንደተጣሰ አስመስሎ ማስተጋባቱ ላይ ነው፡፡

## IV. መንግስት የሚያበረታታው ወይም የሚያጣጥለው ኃይማኖት የለም!

ከላይ በአጭሩ ለማየት እንደተሞከረው በሀገራችን እንደመንግስት አንድን ኃይማኖት ደግፎ ሌላውን መንቀፍ የሚቻልበት ሁኔታ ዝግ ነው፡፡ የየኃይማኖቱን አስተምህሮዎች መልክ የማስያዝ ጉዳይ የእያንዳንዱ ኃይማኖት ተከታዮችና ተቋሞቻቸው ጉዳይ ነው፡፡ የመንግስት ድርሻ ሜዳው ለሁሉም እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ በሜዳው መሮጥ፣ መራመድና መተኛት የእያንዳንዱ ኃይማኖት አማኝ ጉዳይ ነው፡፡

ኃይማኖት በመንግስት ጣልቃ የሚገባባቸው ሁኔታዎች በህገ-መንግስቱ ዝግ ቢሆኑም በተግባር ከማንኛውም ወገን የሚከሰቱበት ሁኔታ እና ተጨባጭ አደጋና ተግባር ሲኖር በወቅቱ ማረምና መልክ ማስያዝ በኃይማኖት ጣልቃ መግባት ሊሆን አይችልም፡፡ በተመሳሳይ አነጋገር አንድ ኃይማኖት በሌላ ኃይማኖት ጣልቃ በሚገባበት ጊዜ ሥርዓት ማስያዝም መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል ሊያስብል አይችልም፡፡ ህገ-መንስቱን ማስከበር ማለት ይህ አለመፈፀሙን ማረጋገጥና ሲፈፀምም ማስተካከል ማለት ስለሆነ፡፡ ይልቁንም ጣልቃ የተገባበትን ብቻ ሳይሆን በመሰረቱ ለጊዜው ጣልቃ የገባውንም

ኃይማኖት የእኩልነት መብትና እሱም በተራው በሌላ ኃይል ጫልቃ እንዳይገባበት የሚደነግገውን የህገ-መንግስቱን ድንጋጌ ማስከበር ነው፡፡

ከላይ የተገለፀው አጠቃላይ አባባል እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ኃይማኖት ዙሪያ የኃይማኖቱ አስተምህሮ ከሚያዘው ውጭ በሆነ የተወሰነ ወገን የሚንፀባረቅ አክራሪነትን መጠቀምና ማጋለጥ እንዲሁም መታገል በዋነኝነት የእምነቱ ተከታዮች ኃላፊነት እና ግዴታ ነው፡፡ በጠባቡ ከታየ የራሳቸውን ኃይማኖት ኃይማኖቱ ከሚያዘው መንገድ ከሚያፈነግጡ ኃይሎች ለማጽዳት ይጠቅማቸዋል፡፡ ዞሮ ዞሮ በአንድ ኃይማኖት ዙሪያ የሚፈጠር ፅንፈኝነት በቅድሚያ በዚያው ኃይማኖት ውስጥ አፈናና ብጥብጥ በማስነሳት ነው የሚጀመረው፡፡ በአብዛኛው በከዋርጂያና ወሃቢያ የተቃጠሉት መስጂዶችና የታዋቂ ሀገራችን የኃይማኖት መሪዎች (አባቶች) የመቃብር ሥራዎች ጥፋት ያነጣጠረው በቅድሚያ በሙስሊሙ ላይ ነው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ነው ቤተክርስቲያናትን ማቃጠል የጀመሩት፡፡ ለነገሩ ከየትኛውም ቢጀመር በየትኛውም እምነት ተከታይ ቢጠናቀቅ ፀረ-ሰላምና ፀረ-ዴሞክራሲ ነው፡፡ ስለሆነም ፀረ-ህገመንግስት ነው፡፡ ሰፋ ተደርጎ ሲታይ ደግሞ በአንድ ኃይማኖት ውስጥ የተጀመረው አፈናና አለመረጋጋት በዚያ ኃይማኖት እና በሌሎች ኃይማኖቶች መካከል የነበረውን መከባበርና መቻቻል በማፈራረስ የትኛውንም ኃይማኖት በነፃነት መከተል የሚቻልበትን እድል ወደ ማጨለም መስፋፋቱ አይቀርም፡፡ ይህም ሄዶ ሄዶ የዜጎችን የተናጠልና የጋራ መብቶች (የፈለጉትን እምነት የመከተል መብትን ጨምሮ) መንፈግ ነው፡፡ ሌላኛው ወገን ይህን ትንኮሳ በፀጋ ለመቀበል የሚኖረው ትዕግስት ገደብ የሚኖረው መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህም በአፀፋ የመመለስ ሁኔታ ይከተላል፡፡ ይህም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለውንም የሌለውንም ዜጋ ሁሉ የሚያተራምስ የሰላምና አብሮ የመኖር ጠንቅ መሆኑ አይቀርም፡፡

ሁልጊዜም ፅንፈኞች ማንኛውም ሰው በሚከተለው እምነት የግል መብት የለውም ብለው ያምናሉ፡፡ ውይይትና መግባባት፣ ሰላማዊ ክርክርን በማውገዝ በአመጽ ተደግፈው የራሳቸውን አተያይ ይጭናሉ፡፡ ከፍቅር ጥላቻን፣ ከርህራሄ ጭካኔን፣ ከመቻቻል መናቆርን፣ ከእውቀት ድንቁርናን፣ ከውይይት ጉልበትን ይመርጣሉ፣ ያበረታታሉ፡፡ ጽንፈኞች የራሳቸውን አመለካከት ማንም ሃይ ባይ በሌለበት አኳኋን ማራመድ እንዲችሉ ሌሎች አመለካከቶች ሁሉ መዳፈን እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡ ፅንፈኞች የመንግስትና የኃይማኖት መለያየትን አይቀበሉም፡፡ ይልቅ የነሱ እምነት የተለየ የበላይነት እንዲኖረውና መንግስታዊ ድጋፍና ጡንቻ እንዲኖረው ይፈልጋሉ፡፡ ይህ አመለካከት በሁሉም ኃይማኖቶች የሚስተዋልና በተለያየ መልክና ደረጃ የሚንፀባረቅ ነው፡፡

በሀገራችን ዜጎች በሚከተሉት ~~እምነት ምክንያት በሚገፋባቸው፣ ተገደው~~ የሌላውን ኃይማኖት ካልተከተሉ ክንብረት ክቀያቸው በሚፈናቀሉባቸው፣ በሚከተሉት እምነት ምክንያት በተወሰኑ የመንግስት መ/ቤቶች ተቀጥረው ሀገራቸውን የማገልገል፣ ከተቀጠሩም ከመሰላሉ ስር ፈቀቅ እንዳይሉ ይደረግባቸው በነበሩ በነዚያ ህገ-መንግስታዊና መንግስታዊ ጥበቃ የነበራቸው ግፎች በነገሱባቸው የጨለማ ዘመናት እንኳን ጠንክሮ የዘለቀውን የኃይማኖቶችን መከባበርና መቻቻል፣ የህዝቦችን አብሮ የመኖር እና መደጋገፍ ትስስር ለመበጣጠስ በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጽንፈኛ/አክራሪ ኃይሎች የተፈፀሙ የጥፋት ድግሶችን ማስተዋል ጥሩ ነው። ጥፋቶቹ ማተራመስ የጀመሩት በቅድሚያ የወጡባቸውን ኃይማኖት ተከታዮች ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው የተቃጠሉና የፈረሱ መስጂዶች፣ የታዋቂ የእስልምና ኃይማኖት መሪዎች የመቃብር ስፍራዎች በሙሉ ጥፋት የተፈፀመባቸው እስልምናን እንከተላለን በሚሉ ጥቂት ፅንፈኞች ነበር። የሙስሊሙን ተቋማት ከማፈራረስ ሳይቦዝኑ ቤተክርስቲያናት አውድመዋል። በክርስትና በኩልም ሌላውን የሚያንቋሽሹ፣ የተለያዩ የክርስትና ተከታዮችን ጨምሮ መናፍቃን፣ ኢ-አማንያን በማለት የሚተነኩሱ ኃይሎች አሉ። ከሁሉም ኃይማኖቶች አንፃር ያሉት እነዚህ ፅንፈኞች በርካታ ንፁሃን ዜጎችን አሳስተው በማነሳሳትና አንዱ በሌላው ለመዝመት የተዘጋጀ በማስመሰል የፍጥጫ ድባብ እንዲነግስ የሚሰሩ ናቸው። በእርግጥ ከበርካታዎቹ በስተጀርባ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስፖንሰሮች ያሉዋቸው የፖለቲካ አጀንዳ የተላበሱ ጽንፈኞች ናቸው። ብዙሃኑ ግን ለእምነታቸው ዘብ የቆሙ እየመሰላቸው በቀላሉ ሊሳሳቱ ይችላሉ።

እንግዲህ በአንድ በኩል የዘመናት የህዝባችንን የመብት ጥያቄ መልሰን፣ ለዘመናት ሀገራችን ከምትታወቅበት የድህነትና ኋላቀርነት ስምጥ ገድል እየወጣን አንገታችንን ቀና በማድረግ በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ ቀድሞ በምንታወቅበት ሳይሆን በአዲሱ ገፅታችን መታየት ጀምረናል። ይህም ገና ጅምር በመሆኑ ቀንና ማታ ይህንኑ ለማስፋት እንዋደቃለን። በሌላ በኩል የዞረ ሂሳባቸውን ለማወራረድ ያሰፈሰፉና አዳዲስ ፍላጎቶች የፈጠሩዋቸው የጥፋት ኃይሎች የተገኘውን ሰበብ ሁሉ በመጠቀም እያመለጥነው ወዳለነው ገደል ሊከቱን እየባጁ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን። ስለዚህ በድህነት ላይ የጀመርነውን ዘመቻ እያጧጧፍን፣ ከየትኛውም ኃይማኖት ይሁን ፖለቲካ ጫፍ የሚነሳን ጽንፈኝነትን እንደ መንግስት ይሁን እንደ ዜጋ በማጋለጥ መጪ ተስፋችንን ይበልጥ ብሩህ ማድረግ የሁላችንም ግዴታ ነው። በማንኛውም ሴክት ውስጥ የሚታይ ይህን የመሰለውን ፅንፈኝነት ማጋለጥ ሴክቱን የሚከተሉትን ዜጎች እምነት ነጻነት መጋፋት አይሆንም። በዚህ እይታ ሰሞኑን ከተፈጠሩት ብዥታዎች አንዱ መንግስት የወሃቢያ ሴክትን በማጥፋት አህባሽ እንዲጠናከር ይሰራል በሚል

በጽንፈኛ ኃይሎች ሆን ተብሎ የተራገበውንና በርከት ያለ ሰው ለማደናገር የቻሉበትን ሁኔታ ማየት ተገቢ ነው፡፡

ወሃቢያን ወይም ሌላውን የመከተል መብት የዜጎች ነው፡፡ መንግስት ሊመርጥላቸው አይችልም፡፡ እስከአሁን ከደረሱ ጥፋቶች በስተጀርባ ጠንከር ያለ የውሃቢያ እምነት የሚከተሉ ግለሰቦች መኖራቸው ግን እርግጥ ነው፡፡ ከዚሁ ውስጥም እስላማዊ ባልሆነ መንግስት የሚመራ ሀገር ሊኖር አይገባም፣ ስለዚህም መንግስትን በኃይል በማዳከም በሸሪዓ እንዲተዳደር ማድረግ አለብን የሚል ጽንፍም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚራመድ ነው፡፡ ይኸው አቋም ከእስልምና ኃይማኖት ውጪ ሌላ ኃይማኖት የሚከተሉትን ብቻ ሳይሆን ከሙስሊሙም ነባር ተቋማትን በማውደም የእስልምና እምነት ተከታዮች ያመኑባቸውን የእምነቱን ተግባሮች በነፃነት እንዳይፈፅሙ በማወክ የሚገለፅ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተግባራት ደግሞ ፀረ-ህገ መንግስት ናቸው፡፡ ወሃቢያ ይሁን ሌላ እምነት ተከታይ ፀረ-ህገ መንግስት አቋሞቹንና ተግባሮችን አውግዞ እንደማንኛውም ዜጋ ወይም ቡድን የራሱ መብት እንዲከበርለት እንደሚፈልገው ሁሉ የሌላውንም መብት አክብሮ እስከተንቀሳቀሰ ድረስ ከህገ-መንግስቱ ጋር በማይጋጩትና የእምነቱ አስተምህሮት በሆኑት ጉዳዮች ላይ መንግስት የመምረጥም፣ የመተቸትም መብትም ፍላጎትም የለውም፡፡ ይህን አድርጎም አያውቅም፡፡

በማንኛውም ኃይማኖት ወይም ሴክት ወይም አካል ቢፈፀም የመንግስታዊ ይሁን ኃይማኖታዊ ተቋማትን ማውደም ፀረ-ህገ መንግስት አቋምና ተግባር ነው፡፡ የራስን አመለካከት ያልተከተለውን በአንድ ወይም በሌላ ለማንበርከክ መሞከር ፀረ-ህገ መንግስታዊ ነው፡፡ የሀገሪቱን ህጎች በሁለመናው ላለማክበር የሚደረግ እንቅስቃሴ ህገ-ወጥነት ነው፣ የሌላውን ኃይማኖት ይሁን የዚያኑ ኃይማኖት ሌሎች ተከታዮችን በህትመት ይሁን በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በህቡዕ ይሁን በይፋ በማሰራጨት ማንቋሸሽ ፀረ-ህገ መንግስታዊ ነው፡፡ እነዚህን አቋሞችና ተግባሮች ከማጋለጥና ከመዋጋት ለአፍታም ቢሆን አንቦዝንም፡፡ በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የማያሻማ አቋም ይዞ፣ በተግባርም ተገዢ እስከሆኑ ድረስ ወሃቢያ ይሁን ሌላ እምነት እንደ አንድ የዜጎች የኃይማኖት መገለጫ በህጋዊነት ከመንቀሳቀስ የሚከለክለው የለም፡፡ በሁለቱ መካከል ግን የማይታለፍ ግልጽ መስመር አለ፡፡ በነዚህ ሁለት ጫፎች መካከል ያለውን መስመር በደማቁ በማስመር ከሩቁ የሚታይ ማድረግ የትኛውንም እምነት መንካት፣ በየትኛውም ኃይማኖት ጣልቃ መግባት ሊሆን አይችልም፡፡

## V. ራሳችንን ተከላክለን ለህዝቡ እውነቱን ከማስጨበጥ አንፃር ክፍተቶች ነበሩን

ሁኔታውን ጠንቅቀው እያወቁ የራሳቸው የተለየ አጀንዳና አቋም ያላቸው ኃይሎች በኤሌክትሮኒክስ ይሁን በህትመት ሚዲያ፣ በአሜሪካ የስልክ መልክዕክቶች እንዲሁም በበራሪ ወረቀቶችና በሰው ለሰው ግንኙነት በበተኑት የታሰበበትና በቅንጅት በተፈፀመ ዘመቻ በበርካታ ወገኖች ዘንድ አባላችንን ጨምሮ መደናገር ተፈጥሯል:: መንግስትና ድርጅታችን ከመርህ የወጣ ነገር አለመፈፀማቸውንና እንደማይፈፅሙ እርግጠኞች ናቸው:: መጅሊሱ ምን እንደፈፀመና ለምንና እንዴት እንደሄደበት ለህዝበ ሙስሊሙ የማስረዳት ኃላፊነቱ የራሱ ሆኖ መንግስት ግን ቢያንስ የራሱን ድርሻ በወቅቱ በዝርዝር ማስረዳት አለመቻሉ ለነዚህ ኃይሎች አፍራሽ ዘመቻ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል:: የአፍራሽ ኃይሎችን የሀሰት ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ በወቅቱ በተመጣጣኝ ሁኔታ ለመመከት የሚያስችል ለህዝቡ ትክክለኛውን ተግባር የሚያሳይ የፖለቲካና የኮሙኒኬሽን አግባብ ተነድፎ በተቀናጀ ሁኔታ አለመፈፀሙ፣ በዚህ ምክንያት አባላችንና ህዝቡም ለሀሰት ፕሮፖጋንዳው በሰፊው እንዲጋለጡ መፈቀዱ እንደክፍተት መወሰድ የሚገባው ነው::

የአፍራሽ ኃይሎች ዘመቻ አንድ ነገር ሆኖ ብራሳችን በኩል ወጥ የሆነ ግልፅነት በመላው-አባላትና አመራር አካላት ዘንድ ፈጥረን አለመግባታችን የራሱን አሉታዊ ሚና ተጫውቷል:: እየተፈጠረ የነበረውን መደናገር ተገቢውን ሚዛን ሰጥቶ በወቅቱ በማጥራት በኩል የነበረው ክፍተት ቀላል አልነበረም:: በተግባር አፈጻፀም ሂደት በዝርዝር ሲፈተሹ የሚገባቸው የአገላለፅ ይሁን አያያዝ ክፍተቶች እንደሚኖሩም መገመት ይቻላል:: በመሆኑም የአፍራሽ ኃይሎችን ሴራ በወቅቱና በተገቢው ለማጋለጥ በሚያስችለን ደረጃ የተቀናጀ ሥራ አለመሰራቱ ሊስተካከል የሚገባው ነው::

ሰፊው ህዝብ እምነቱ ይበልጥ እንዲጎለብት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ውጪ ጥቅሙ ያልተነካ መሆኑን ማሳየት አለብን:: ሆን ብለው ለተለየ ፅንፈኛ አቋማቸው ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር አልመው ቀንና ማታ በሚዘምቱትና መንግስት እንደመብትም እንደግዴታም በሰራውና ሊሰራው በሚገባው እንዲሁም ኢ-ህገ መንግስታዊ በሆነ መልኩ አንዱን እምነት ደግፎ ሌላውን ለመጣል በሚደረግ ጣልቃ ገብነት መካከል ያለውን ልዩነት በወጉ ሳይገነዘቡ ቀርተው በተደናገሩ፣ እንዲሁም ለጥፋት ኃይሎች ዘመቻ ሰለባ በሆኑት ንፁሃን ዜጎች መካከል የሚታየው የሰልፍ መዛነፍ ትክክለኛ ስፍራውን መያዝ አለበት:: ይህ እንዲሆን በቅድሚያ አባሉና አመራሩ የተሟላ ግልፅነት መያዝ አለበት::

## VI. ቀጣይ የትግል አግባባችን ምን ይሁን

### 6.1 አባላችንና አመራራችን ዘንድ የጋራ ግንዛቤ ይፈጠር

በችግሩ ስፋትና ባህሪይ ዙሪያ-በሁሉም አመራራችን ዘንድ ግልጽነት መኖር አለበት። በዘፈቀደ የሚራመድ አቋምና የሚሰጥ አስተያየት ማስወገድ ያስፈልጋል። ከችግሩ አጠቃላይ ባህሪይ በመነሳት ወደ አጠቃላይ መፍትሔው የምንሄድበት አካሄድ ይኑረን። ከክስተቶች በመነሳት የምንሰጠው አስተያየት፣ ክስተቶቹ ከተከሰቱበት ማህበረሰብ ጋር ብቻ የተቆራኙ መስለው የሚታዩበትን አካሄድ ማስቀረት አለብን፣

ሙስሊሙም ሆነ የሌላ እምነት ተከታዩ አባላችንን በጋራ የሚመለከት ችግር እንደመሆኑ በጋራ ትግል የምንፈታው መሆኑ ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጥ ማድረግ አለብን፣ በምንም ዓይነት ሁኔታ ጥቅል ፈረጃ ውስጥ ከመግባት መቆጠብ ያስፈልጋል፣ የእምነቱ ተከታዮችና ተቋማት በሚፈፅሙትና ሲፈጽሙት በሚገባውና በመንግስት እንደመንግስት ልንሰራው በምንችለውና በሚገባን ጉዳዮች ዙሪያ በተግባርም በአገላለፅም መደበላለቅ እንዳይኖር ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

አባላችንና አመራራችን ከዚህ በፊት በአዲስ ራዕይ ዕትሞች እንደገለፅነው በአንድ በኩል በሚከተለው እምነትና በመንግስትና በህዝብ በተሰጠው ኃላፊነት መካከል የሚኖረውን ድንበር በማደባለቅ ለሚከተለው እምነት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ እላፊ ድጋፍ ሲያደርግ የሚታይበት ሁኔታ በርካታ ነው። ካልሆነም ጥፋት ሲሰራ መሬት ሲወረር፣ በአንዳንድ በዓላት እንደሚታየው ሀገሪቱን የኃይማኖቶች መቻቻልና መከባበር ሳይሆን የፉክክርና የፍጥጫ ማእከል እንደሆነች በሚያስመስል መልኩ የጋራ የሆኑ የመንግስት አደባባዮች፣ ቢሮዎች ወዘተ እንዲሁም የሌላ ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ መኖሪያ ቤቶችና አጥሮች ጭምር በአንድ እምነት ምልክቶችና ሌላውን እምነት በሚነካኩና ህገ-መንግስቱን እና ሌሎች የሰንደቅ ዓለማና ወዘተ ህጎችን በሚፃረር መልኩ መላወሻ ሲያሳጡ አብረው የሚያጯፍሩበት ሁኔታም አለ።

ከዚህ በመጠኑ የተሻሉት ደግሞ ከሚያጠፉት አብረው ጥፋት ሳይፈፅሙ፣ የሚያጠፋውንም ታግለው ሳያስተካክሉ አጥር ጥግ ቆመው የሚመለከቱ ናቸው። ከድርጅታችን መርህ አንፃር ከታየ ሁለቱም ስህተት ናቸው። አብሮ ማጥፋትና፣ ሌላው ሲያጠፋ እያዩ እንዳላዩ ማለፍም ስህተት ነው። ዞሮ ዞሮ በሁለቱም መንገድ ጥፋቶቹ ከመፈፀም የሚገቱበት ሁኔታ አይኖርምና።

ኢህአዴግ የቀሱም የሼኩም ድርጅት ነው። የሆነ ኃይማኖት ተከታይ መሆን ብቻ ሳይሆን ምንም ዓይነት ኃይማኖት አለመከተልም ይቻላል። ስለዚህ ሙስሊም ይሁን ክርስቲያን አባላት ይህን ተከተሉ ያንን አትከተሉ የሚባሉበት ሁኔታ የለም። በርካታ አባላት ማህበረ

ቅዱሳን እንደሆኑት ሁሉ በርካታ አባላትም የወሃቢያ ይሁን የሌላ እምነት ተከታዮች እንዳሉ ይታወቃል። ችግሩ ያለው የትኛውን እምነት ይከተሉ የሚለው አይደለም። ችግሩ ያለው ከሚከተሉት እምነት ወይም ሴክት ውስጥ መቻቻልን፣ ህገ-መንግስትን ሴኩላሪዝምን የሚሸረሽሩ ዝንባሌዎችን ከራሳቸው ይሁን ከሌላው እምነት በተንፀባረቀ ጊዜ ሁሉ ከሚታገሉለት ድርጅት መርህ እና ከሀገሪቱ ህገ-መንግስት መንፈስ አንፃር በጥብቅ ዲሲፕሊን የማይታገሉ መሆናቸው ነው። ለዚህ ነው እምነታችንን በመከተልና የኢህአዴግ አባል ሆኖ በመታገል መካከል ቅራኔ የለም የምንለው። በዚህ መንፈስ ነው አባላችን የሚጠበቅበትን ሚዛናዊነት ይዞ ህገ-መንግስቱ እንዳይሸራረፍ እንዲታገል መጠየቅ እምነቱን እንዲሸረሸር መገደድ ተደርጎ ሊወሰድ የማይገባው።

ነገር ግን የኢህአዴግ አባል የእምነት ነፃነት አለው ሲባል ፀረ-ህገመንግስት አቋሞችን የሚያራምድ ድርጅት ወይም በኃይማኖት ሽፋን የሚካሄድ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ አለበት ማለት አይደለም። በአንድ ጊዜ ሁለቱንም መሆን ስለማይችል መምረጥ የግድ ይላል። ለምሳሌ ወሃቢያ ከእስልምና መሠረቶች የሚከተላቸውን ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች የኢህአዴግ አባል ሆኖም ቢሆን መከተል ችግር የለውም። በተጨባጭ ግን ወሃቢያ ከእስልምና እምነት ፈንጠር ያሉ ጸረ-ህገመንግስታዊ ይዘት ያላቸውና በተጨባጭ ፖለቲካዊ አቋሞች እንዳሉት ጠቃቅሰናል። እነዚህን አቋሞች ሳይተነትን የዚህ ቡድን አባል ሆኖ ካልሆነ በስተቀር በትክክል በእውቀት ላይ ተመስርቶ ካያቸው በአንድ ጊዜ ለህገ-መንግስቱ እየታገለ በሌላ ጎኑ ህገ-መንግስቱን የሚጣረስ አቋም ሊይዝ አይችልም። በአካል ኢህአዴግ ውስጥ ቢሆንም በተግባር ኢህአዴግ መሆኑ ያቋርጣል። በክርስትና ውስጥም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የተዋቀሩ ቡድኖች ከመሠረታዊ የእምነቱ አስተምህሮ ፈንጠር ያለ እና በመሠረቱ ፀረ-ህገመንግስት መገለጫ ያላቸው አቋሞች የተላበሱበትና አንዳንድ የእኛ አባላትና አመራሮችም ኢህአዴግነትንም ፀረ-ኢህአዴጋዊ አቋሞች የያዙ ቡድኖችንም የሚያንቀሳቅሱበት ሁኔታ በገሃድ የሚታይ ነው። ስለዚህም በዚሁ አግባብ ግልፅነት ተፈጥሮ አባላችንና አመራራችን ስልፋን ያስተካክል፣ ለማስተካከል የሚቸገር ግን በሰበባ ሰበብ ሳይሸፋፈን ከድርጅቱ መፅዳት አለበት።

## 6.2 የአክራሪነቱን ኮር ኃይል እና በቅንነት የተቀላቀለውን የሚለይ አካሄድ ይኑረን

ጅምላ ፍረጃ ማስወገዳችን አንድ ነገር ሆኖ በየደረጃው የሰከነ ውይይት እንዲካሄድ ማድረግ ይገባል። በሚዲያ የተጀመረውን ውይይት በጥንቃቄ በመምራት ህዝቡ በአጠቃላይ ስዕሉና በዝርዝር ክስተቶች መካከል ያለውን ልዩነት እንዲገነዘብ ማድረግ አለብን። ለዘብተኛ አቋም ያላቸው በሰፋት የሚዲያ አክሰስ እንዲያገኙ ከምናደርገው ስራ ጎን ለጎን ዕንፈኞቹም እንዲፋጠጡ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። የተሻለ ግልፅነት ያላቸው የእምነቱ ተከታዮች በብዕር ስም ይሁን በይፋ በህትመት ሚዲያዎች በስፋት እንዲሳተፉ ማድረግ ሰፊው ህዝብ የተሻለ

ግንዛቤ እንዲይዝ ማድረግ ያስፈልጋል። ከወሃቢያ ይሁን ከሌላው እምነት ውስጥ ፅንፈኝነት አይመለከተኝም የሚለው በግላጭ ወጥቶ እንዲያወግዝ እድል ሊኖረው ይገባል። በዚሁ አግባብም ልናደፋፍረውና ፅንፈኛው ተነጥሎ እንዲጋለጥ የሚያደርግ አካሄድ ሊኖረን ይገባል።

## 6.3 ከኪራይ ሰብሳቢነት ነጥለን አክራሪነትን መዋጋት አንችልም!

አክራሪነትን ከኪራይ ሰብሳቢነት ጋር አስተሳስረን እንፋለመዋለን ስንል ትግሉ በመሰረቱ የተደራጀ የፖለቲካ ትግል መሆኑን መቀበላችን ነው:: በተናጠል የምናካሂደው ሳይሆን ትግሩ ባለባቸው አካባቢዎች ሁሉ እንደኢህአዴግ የተደራጀ ግምገማ አድርገን በዚህ ላይ የተመሰረተ ትክክለኛ እቅድ ይዘን በጋራ የምንዘምትበት ይሆናል ማለት ነው:: ያልተደራጀና የተበታተነ ትግል ለከፋ ውድቀት ይዳርግ እንደሆነ እንጂ ምንም ፋይዳ እንደማይኖረው በውል ተገንዝበናል ማለት ነው:: ትግሉ የፖለቲካ ትግል ማለትም የአስተሳሰብ ትግል መሆኑን ሊሰመርበት ይገባል:: የትግሉ አላማ አማራጭ ትክክለኛ ዋፖለቲካ አስተሳሰቦችን አቅርቦ አክራሪ አስተሳሰብን በመመከትና በማምከን ተሳስተው የተቀላቀሉ ሃይሎችን ከካምፑ የምናስወጣበት ዋነኛ አንቀሳቃሾቹን የምንነጥልበት ስራ መስራት ነው::

አክራሪነትን በአስተዳደራዊ መልኩ መፋለምና እንደ ፖለቲካ ትግል ወስዶ መንቀሳቀስ ልዩነቱ የሚታየውም እዚህ ላይ ነው:: አስተዳደራዊ ትግል ህገወጥ ተግባርን አጥርቶ የመቅጣት ወይም የማስተካከል ተልዕኮ ያለው ነው:: ፖለቲካዊ ትግል ከህገ ወጥ ተግባሩ በስተጀርባ ያለው አመለካከት ለይቶ በማክሸፍ ብዙሃኑን ከህገወጥ ተግባር ነፃ እንዲሆኑ ማድረግና ዋነኞቹን የመነጠል ተልዕኮ ያለው ነው:: ውጤታማ ስራ ሊሰራ የሚችለው አክራሪነትን በብቃት መመከት የሚቻለው በአስተሳሰብ ትግል በፖለቲካ ትግል አማካኝነት ነው:: የፖለቲካ ትግሉ ከተሳካ የተነጠሉትን አንቀሳቃሾች ለይቶ በህገ ወጥ ተግባራቸው ተጠያቂ በማድረግ ትግሉን በይበልጥ ስኬታማ ማድረግ ይቻላል:: ፖለቲካዊ ትግሉ ካልተሳካ ግን አስተዳደራዊ ትግሉ ቢካሄድም ዘላቂ ውጤት አይኖረውም::

## 6.4 ዘላቂው የፀረ- አክራሪነት ትግል ድንቁርናና ድህነትን ማጥፋት ነው:: ከጀመርነው የህዳሴ መስመር የተለየ የስኬት መንገድ የለም!

የአገራችንን ህዝቦች ለአክራሪነት ተጋላጭ የሚያደርጋቸው ነገር ድህነትና ኋላቀርነት ነው:: ህዝባችን ድህነት ወጥሮ ባይዘው የጨነቀው እርጉዝ ያገባል እንዲሉ ለተለያዩ የጥፋት አመለካከቶች ተጋላጭ ባልሆነ ነበር:: ህዝባችን የተለያዩ ኋላቀር አመለካከቶች ባይጠናወቱት፣ የዴሞክራሲ ባህሉና አስተሳሰቡም የላቀ ደረጃ ላይ ቢደርስ ኖሮ ለተለያዩ የጥፋት አመለካከቶች ለኪራይ ሰብሳቢነት ጭምር ተጋላጭ ባልሆነ ነበር:: የአክራሪነትን አስተሳሰብ ከምንጩ የምናደርቀው የህዝባችንን ተጋላጭነት ስናስወግድ ነው:: የህዝባችን ተጋላጭነት የምናስወግደው የጀመርነውን የልማት ትግል በመቀጠልና ህዝቡ ከዚሁ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ከአስጨናቂውና ወደ ጥፋት ጎዳና ሊመራው ከሚችለው ድህነት ስንገላገለው ነው::

ህዝባችንን ከኋላ-ቀር አስተሳሰቦች ነፃ ማውጣት የምንችለው ትምህርትን ስናስፋፋ፣ የትምህርቱ ሳይንሳዊ ይዘትና ጥራት እንዲረጋገጥ ስናደርግ ነው:: የዴሞክራሲ ስርአታችንን በተግባር እውን በማድረግ፣ የዴሞክራሲ ባህልን ለማስፋፋት የማያቋርጥ ትምህርት በመስጠትና እነዚህን በቀጣይነት በማሻሻል ነው አክራሪነትን ጨምሮ ሌሎች ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦች ህዝባችንን ከፉኛ ሊፈታተኑ ከሚችሉበት ሁኔታ ልንላቀቅ የምንችለው::

የልማትና የዴሞክራሲ ጎዳናችን የአገራችን ችግሮች ሁሉ መሰረታዊና ዘላቂ መፍትሄ ነው:: የአክራሪነት ችግርን የህዝባችንን ተጋላጭነት በማስቀረት ከስሩ የምናደርቅበት መንገድ ሌላ ሳይሆን ይኸው የሁሉም ችግሮቻችን መፍትሄ ነው ብለን የተቀበልነው የልማትና የዴሞክራሲ መስመራችን ነው:: እናም ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ ሀገራችን እንደሌሎች አገሮች በሃይማኖት አክራሪነት እንዳትተራመስ ለመታደግ ስንል የጀመርነውን የልማትና የዴሞክራሲ ትግል ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክረን በመቀጠል ዳር ማድረስ ይገባናል::

አክራሪነት በአገራችን ሊስፋፋ የሚችለው በአንድ በኩል ህዝባችን በእንደዚህ አይነቱ አመለካከት ተጋላጭ እንዲሆን የሚያደርጉት ነባራዊ ሁኔታዎች በመኖራቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእነዚህ ነባራዊ ሁኔታዎች በመጠቀም የሚያራግቡት የኪራይ ሰብሳቢነት ሃይሎች ስላሉ መሆኑ ተገልጿል:: ተጋላጭነታችንን ለማስቀረት ነባራዊ ሁኔታውን ለመቀየር ምን መስራትና በምን አቅጣጫ መታገል እንዳለብንም ግልፅ ሆኗል:: ከዚሁ ጎን ለጎን አክራሪነትን የሚያራግቡ የኪራይ ሰብሳቢነት ሃይሎችን ከአክራሪነት ጋር ደርበን መታገል ይኖርብናል:: እነዚህን ሃይሎች ዛሬውኑ በየዕለቱ በብቃት ካልታገልናቸው ዘላቂው መፍትሄ በነዚህ የጥፋት ሃይሎች ተልዕኮ ሊሰናከልና ተግባራዊ ሳይሆን ሊቀር ይችላልና::

አክራሪነትን ከኪራይ ሰብሳቢ ሃይሎች ነጥለን መታገል አንችልም ስንል እያንዳንዷን የአክራሪነት እንቅስቃሴ ከበስተጀርባ ሆነው የሚያራግቡ ሃይሎች እነማን እንደሆኑ አጥርተን በማወቅ ይህንኑ ሃቅ ለህዝቡ በማስረዳት የአክራሪነቱ እንቅስቃሴ በዋናነት አንድን የፖለቲካ አላማ በማራመድ የከሰሩ የፖለቲካ ሃይሎች የሚያራምዱት ተልዕኮ እንጂ ከሃቀኛ የእምነት ነፃነት ጋር ምንም የሚያስተሳስር ነገር እንደሌለው ማስጨበጥ አለብን ማለት ነው:: ይህንኑ ደግመን ደጋግመን በማስረዳት የአክራሪነት እንቅስቃሴና የከሰሩ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካ ሃይሎች የማይነጣጠሉ የጥፋት ሃይሎች መሆናቸውን በጥብቅ እንዲያምንበት ከዚህ በመነሳትም ማንኛውም የአክራሪነት እንቅስቃሴ በትክክለኛ ገፅታው ተገንዝቦ እንዲመከተው ማድረግ አለብን ማለት ነው::

አክራሪነትን ከኪራይ ሰብሳቢነት ነጥለን መታገል አንችልም ስንል ኪራይ ሰብሳቢ ሃይሎች የሚያነሷት እያንዳንዷ አክራሪ ጥያቄ በህገ መንግስቱና ከዴሞክራሲ መርሆዎች ተነስተን ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-የእምነት እኩልነት መሆኗን፣ ከልማትና ሰላም አጀንዳችን

ተነስተን ፀረ-ልማት መሆኗን ማጋለጥ አለብን ማለት ነው። አክራሪነትን የምንፈርጀው ከልማትና ከዴሞክራሲ መስመራችን ተነስተን በመሆኑ እንደኢህአዴግ አክራሪነትን ስንታገል በሃይማኖታዊ ክርክር እንካሰላንቲያ ውስጥ መግባት አንችልም አይገባም። ያንን መስራት የሚችሉትና የሚገባቸው የሃይማኖት መሪዎችና ሊቃውንት ናቸው። እኛ ከህገ መንግስቱና ህገ መንግስቱ በሃይማኖት ዙሪያ ካስቀመጣቸው መርሆዎች በመነሳት ነው ልንፋለም የምንችለው። እነዚህ መርሆዎች ዴሞክራሲያዊና ከሁሉም ሃይማኖቶች ጋር አብረው የሚራመዱ መሆናቸውን በማሳየት አክራሪነት እነዚህን መርሆዎች በመፃረሩ ፀረ-ዴሞክራሲ ፀረ-የእምነት ነፃነትና እኩልነት በመሆኑ ይህንን በተጨባጭ በማጋለጥ ነው። እኛ ከልማትና ሰላም አጀንዳችን በመነሳት ነው ልንፋለም የምንችለው። ይህ አጀንዳ የሁሉንም እምነቶች ጥቅም የሚያስጠብቅና ከሃይማኖታዊ መርሆዎችም ጋር አብሮ የሚራመድ መሆኑን በማሳየት አክራሪነት ይህንኑ አጀንዳ በመፃረር ፀረ-ሰላም ፀረ-ልማትና ፀረ-የእምነት ነጻነትና እኩልነት መሆኑን በማጋለጥ ነው መፋለም የምንችለው።

## 6.5 ትግላችን ህገ-መንግስቱን ማዕከል ያደረገ ይሁን

በዚህ ፅሁፍ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ህገ-መንግስታችን ለግለሰብና ለቡድን መብቶች አስተማማኝ ጥበቃ የሰጠውን ያክል እነዚህን መብቶቻችንን ለመተግበር በምንቀሳቀስበት ጊዜ ልንከተላቸው የሚገቡ መርሆችና ዳር ድንበሮችንም በዝርዝር አስቀምጧል። አሁን የተፈጠረውን ብሄርታም ሆነ ማንኛውንም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባርና ዝንባሌ የምንታገልባቸው መሳሪያዎቻችን በዋነኛነት በህገ-መንግስቱ ማዕቀፍ ውስጥ ተዘርዝረዋል። አክራሪነትም ይሁን ማንኛውንም የህገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች የመናድ ውጤት የሚኖራቸውን አፍራሽ እንቅስቃሴዎች ለመከላከል የምናደርገው እንቅስቃሴ በእግረ መንገዱም በዘላቂነት በህገ-መንግስታችን ዙሪያ የተሻለ ግልፅነትና መግባባት መፍጠር በምንችልበት አግባብ መሆን አለበት። ይህንን ማድረግ ሳንችል ዜጎች በአንድ በኩል ህገ-መንግስቱ ያረጋገጠላቸውን መብት እየጠየቁና በዚህ መብታቸውም ለመጠቀም እየተንቀሳቀሱ እዚያው ሳሉ የሌሎችን መብት የሚዳምጡበትን ፀረ-ህገመንግስታዊ ተግባር እንዳይፈፅሙ እና ፈፅመው ከተገኙም ጥፋት መሆኑን አውቀው እንዲመለሱ ማድረግ አይቻልም። ዜጎች በኃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ አቋም ያላቸው ቡድኖችን የአክራሪነት አደጋ በውል ተገንዝበው በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲፋለሙት ማድረግ የሚቻለው ህገ-መንግስቱ ያረጋገጠላቸው መብት ምን እንደሆነና ይህንንም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ማጣት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሊረዱት ሲችሉ ነው።